አባ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ጳጉሜ 05/2008 ዓ/ም

## የአዲስ ዘመን መለወጫ ቃለ ምዕዳን!

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በሀገራችን በኢትዮጵያና በመላው ዓለም የምትገኙ ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳት ፥ ማኅበረ ካህናት ፥ ምእመናን እና ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያት ሁሉ እግዚአብሔር በቸርነቱ እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ 2009 ዓ/ም አደረሳችሁ።

*«አቤቱ አንተ ለዘላለም ትኖራለህ ፤ ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው ። ስለ ምን ለዘላለም ትረሳናለህ ? ስለ ምንስ ለረጅም ዘመን ትተወናለህ ? አቤቱ ፥ ወደ አንተ መልሰን ፤እኛም እንመለሳለን ፤ ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ።» /ሰቆ ኤ 5 ፥ 19-22/ ።*

ዓመታት ፥ አውራኅ ፥ ሳምንታት ፥ ዕለታት ፥ ሰዓታት ሁሉ የእግዚአብሔር ገንዘቦች ናቸው ። ጊዜና ዘመን ያላስገኘው ፥ ዘመንና ጊዜን ያስገኘ ፣ ቅድመ ዓለም የነበረ ፣ አሁንም ያለ ፣ ወደ ፊትም ይህን ዓለም አሳልፎ የሚኖር መንግሥቱም የማይሻር እግዚአብሔር ብቻ ነው ። እግዚአብሔር በቸርነቱ ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ ስላሸጋገረን እናመሰግነዋለን ።

ዓመተ ምሕረት ማለት በክርስቶስ ሰው መሆን ምክንያት ክብራቸውንና ነጻነታቸውን የተነጠቁ የሰውልጆች ነጻነትን ያገኙበት ፣ በጠላት ማሰሪያ የታሰሩ የተፈቱበት ፣ የሰውልጅ ክብር የተመለሰበት ዓመት ፣ የምሕረት ዓመት፣ የይቅርታ ዓመት ማለት ነው ። ዓመተ ምሕረት ማለት ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ክርስቶስ ፥ የሰውን ልጅ ባሕርይ ወይም ማንነት ያከበረበትን ዘመን ማለት ነው ። ለዚህ ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለታሰሩት መፈታትን ፥ ለዕውሮች ማየትን ፥ … እሰብከ ዘንድ ፣ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውን ዓመትም እሰብክ ዘንድ ልኮኛል» ያለው ። (ሉቃ 4 ፥ 19)

መንፈሳዊ ነጻነት የሰብአዊ ማንነታችን ነጻነት መገለጫ ነው ። ሥጋዊ ነጻነትም የመንፈሳዊ ነጻነት መገለጫ ነው ። ለሰው ልጅ ሥጋዊና መንፈሳዊ ነጻነቱ ካልተጠበቀለት የደስታ ስሜት አይሰማውም ። ዛሬ አዲሱን ዓመት ስንቀበል የሀገራችን ሕዝብ ነጻነቱን ስለ ተገፈፈ፣ የምሕረቱንም ዓመት አምባገነን መሪዎቹ ዓመተ መዓት/የመዓት ዓመት/ ስላደረጉበት ይኸውና በሀገራችን በኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም የሚገኘው ሕዝባችን በልቅሶና በእንባ ፣ በዋይታና በሰቀቀን አዲሱን ዓመት እንዲቀበል ተገዷል ።

15521Orchard Drive Bowie MD 20715 Phone:(301) 262-3031

እግዚአብሔር እድሜንና ዘመንን የሰጠን እንድንጠፋፋ ሳይሆን እንድንተባበርበት ነው። እንድናንስ ሳይሆን እንድናድግበት ነው ። አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ፈተናወችን እያሳላፈች እስከዚህ ዘመን ደርሳለች ። የወደፊቱን እርምጃዋን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ስለ ሆነ ሁላችንም በጸሎትና በእንባ የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ እያሰብን ተግተን ልንጸልይ ይገባል።

**የተከበራችሁ በሀገራችን በኢትዮጵያእና በመላው ዓለም የምትገኙ የመፈስ ቅዱስ ልጆቻችን!**

አዲሱን ዓመት ዘመነ ማቴዎስን ስንቀበል በሀገራችን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በሕዝባችን ላይ በሚፈጽመው ግፍ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ኀዘን ላይ ናት ። አገራችንም በልቅሶና በሰቆቃ ውስጥ ናት ፤ ሁላችንም ስለ ሀገራችን በከፍተኛ ሀኀዘን ላይ እንገኛለን ።

ይህን አዲስ ዓመት ስንቀበል ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ በጣም አሳሳቢ ስለ ሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ አዲሱን ዓመት፣ ተድላ ሥጋ በማድረግ፣ደግሶ በመብላት፣ በመጠጣት፣በዘፈን፣ በጭፈራ ሳይሆን በጸሎት እና በኀዘን እንድናሳልፈው መሰኑና በመላው ዓለምም ለሚገኘው ሕዝባችን መልእክቱን ማስተላለፉ ይታወሳል ። የቤተ ክርስቲያንን ቃል ያከበራችሁትን እግዚአብሔር ያከብራችሁ ። አሁንም ደግመን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የምናስተላልፈው መልእክት፡-

1) ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ያለፍትሕ ተገድለውባቸው እያለቀሱ ፣ ብዙ ልጆች ወላጆቻቸውን በሞትና በእስራት ተነጥቀው እያነቡ እንዴት አድርገን አዲሱን ዓመት በደስታ ልናከብር እንችላለን ?

2) በአሥር ሽህዎች የሚቈጠሩ አገር ተረካቢ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ያለፍትሕ በማሰቃያ ቦታ ሌትና ቀን እየተገረፉ ፣ በልዩ ልዩ ማሰቃያ ስልት እየተሰቃዩ ፣ በቃል የማይገለጽ፣ በሕሊናም ለማሰብ የሚከብድ ፥ አእምሮን ሰላም የሚነሣ፣ ኢሰብአዊ ግፍ እየተፈጸመባቸው፣የሕሊና እስረኞች በእሳት እየተቃጠሉ ፣ እንዴት አዲስ ዓመትን ምክንያት አድርገን ልንደሰት እንችላለን ?

3) በጎንደርና በባህርዳር በዘመን መለወጫ ዋዜማ ስልክ፣ መብራት እና ኢንተርኔት በመጥፋት፣ በነፍሰ ገዳዩ የህወሀት መንግሥት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ንጹሀን እየታፈሱ፣ ወደማሰቃያ ቦታ እየተጋዙ፣ በጎጃም በብዙ ሺህ የሚቀጠሩ ወጣቶች ታፍሰው በብር ሸለቆ የጦር ካምፕ እየተሰቃዩ፣ በኦሮምኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን ላይ ኢፍተዊ ግድያ ዕለት ዕለት የተፈጸመ፣እናት በልጇ አስከሬን ላይ ተቀመጭ ተብላ መደብደቧን እየሰማን፣የኢትዮጵያ እናቶች በእንባ ብህር ሰጥመው፣ ስለልጆቻቸው ድረሱልን እያሉ እየጮሁ፣ እንዴት በደስታ ዓመት በዓላችንን ለመዋል እንችላለን? ነገር ግን ከሚያለቅሰው ሕዝባችን ጋር እያለቀስን፣ እግዘአብሔር ለሕዝባችን ተገቢውን ፍትሕ እንዲሰጥ በሀዘንና በጸሎት ልናሳልፈው ይገባል።

4) ኢትዮጵያውያን ሆይ! ሕዝብ በአገራችን አዲስ ዓመትን በደስታ ለማክበር የሚቻለው፣ ክብሩ፣ መብቱና ነጻነቱ የተጠበቀለት ሕዝብ ያላት ሀገር ስትሆን ነው ። አዲሱን ዓመት አዲስ ለማድረግ አሮጌውን ገዳይ ሥርአት ተረባርቦ መሻር ያስፈልጋል። ካለፈው ዓመት ጋር የአፈናንና የነፍሰ ገዳዮችን ሥርዓት ማሳለፍ፣ በአዲስ ዓመት፣ በአዲስ ተስፋ፣ ፍትሕ፣ ርትዕ የሰፈነባት ፣ ሕዝቦቿ በእኩልነት የሚኖሩባት ሀገር እንድትሆን ለኢትዮጵያ አንድ ሁኖ መነሣት ያስፈልጋል። ያ ካልሆነ ግን ለሕዝቡ ክብር የሌለው ነፍሰ ገዳይ አካል ትውልዱን ከማጥፋት ስለማይቆጠብ ፥ አንዱ ሲሞት ሌላው ዝም ብሎ ማየት አይገባም ። አንድ ሁኖ ተነሥቶ ስለሚሞቱትና ስለሚታፈኑት መናገር ያልቻለ ሕዝብ የመከራውን ዓመት ያራዝማል፤ ስለዚህ ኢትዮጵያውን በአንድነት ተነስታችሁ ከፉውን ሥራት በበጎ ሥርዐት ስትተኩት ብቻ ነው አዲስ ዓመት ትርጉም የሚኖረው።

5) ስለነጻነታቸው የሞቱን እናከብራቸዋለን፤ የተሰሩትንም ፍትህና እኩልነት የሰፈነበትን አዲት ኢትዮጵያን ለማየት እዲታደሉ እንጸልይላቸዋለን። የሟች ቤተ ሰቦችንም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዲያጽናናልን፣ እንዲሁም ልጆቻቸው ስለ ሀገራችን የከፈሉት የሕይወት ዋጋ ፍሬ አፍርቶ ለማየት እንዲበቁ እግዚአብሔርን እንማጸነዋለን።

6) በዚህ ወቅት በሀገራችን የድሆችን ጩኸት የሚሰማ የለም ፣ የረኃብተኞችን ረኃብ የሚመለከት የለም ፣ የሚገፉትን ሕዝቦች ግፍ የሚያዳምጥ የለም ። ስለዚህ ይህን ሁሉ ወደሚመለከተው የፍትሕ አምላክ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር አገራችንን እና ሕዝባችንን እያሰብን እንደ ኤርምያስ « ስለ ምን ለዘለዓለም ትረሳናለህ? ስለ ምንስ ለረጅም ዘመን ትተወናለህ ? አቤቱ ወደ አንተ መልሰን እኛም እንመለሳለን ፤ ዘመናችንን እንደ ቀድሞው አድስ።» እያልን በአንድነት እንድንጸልይ ጥሪያችንን እናቀርባልን ።

በመጨረሻም:-ይህ ቀን ያልፋል፣ ገዳዮቹም ሆኑ ሥርዐታቸው ያሻራሉ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ምን ጊዜም ገዳዮቹን ድል ነሥቶ፣ ሀገሩንም አስከብሮ በአንድነት እንደሚኖር እግዚአብሔርና ታሪክ ምስክር ናቸው። እግዚአብሔር አዲሱን ዓመት ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነጻነትና በክብር የሚኖርበት፣ የሰላም ፥ የፍትሕ ፥ የአንድነት ዓመት ያድርግልን ።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ ይቀድሳችሁ ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!

አባ መርቆሬዎስ

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ

15521Orchard Drive Bowie MD 20715 Phone:(301) 262-3031